በኅብረተሰብአዊነት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ
ወታደራዊ መንግሥት
የጠቅላይ ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ ።

የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁ. 1202/73
ጥር 17 ቀን 1974 ዓ.ም.

ዳኞች ፡ 1.
2.
3.

ይግባኝ ባይ ፡— ቀና ዳግም ቀረበ

ስለመልስ ሰጭ፡— ውቤ አምዴ ቀረበ

ይህ ጉዳይ በቀጠሮ ያደረው ሁለቱ ወገኖች ጉዳያችንን ከፍርድ ቤት ውጭ በእርቅ እንጨርሳለን ስላሉ ከታረቁ ውጤቱን ይዘው እንዲቀርቡ ነበር ። ነገር ግን ያልታረቁና ክርክራቸውም በእርቅ የማያልቅ መሆኑን ስለገለጡ ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል ።

## ው ሳ ኔ ፣

ይግባኝ ባዩ እጮኛውን ፣ የእጮኛውን እናትና አባት በማጣመር በአውራጃው ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው ተከሳሾቹ የመተጫጨት ውል ያለምክንያት ስላፈረሱ ለእጮኛዬ የሰጠሁትን ጌጣ ጌጦች እንዲመልሱልኝ ፣ ለደረሰብኝ ኪሳራና የሕሊና ጉዳት ብር 10[illegible]0.00 ካሳ እንዲከፍሉኝ በማለት ነው ። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው አውራጃው ፍርድ ቤት የአሁኗ መልስ ሰጭ ከሳሹ የጠየቀውን ካሳ ብር 10[illegible]0.00 እንድትከፍል ፣ ጌጣ ጌጦቹን እንድትመልስ ፍርድ ሰጥቷል ።

ሁለተኛዋ ተከሳሽ ይህን ፍርድ በመቃወም ቅሬታዋን በይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርባ አሰምታለች ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 723/1/ መሠረት የውሉ መፍረስ በመጀመሪያ መታየት ያለበት በቤተ ዘመድ ጉባዔ ስለሆነ አውራጃው ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ እንዳልተፈረደ ሆኖ በዚሁ መሠረት ጉዳዩ እንደገና ይታይ ሲል ወስኗል ። የአሁኑ ይግባኝ የቀረበውም ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው ።

እኛም በበኩላችን ጉዳዩን መርምረነዋል ። እንደመረመርነውም ከፍተኛው ፍርድ ቤት አውራጃው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ የሻረው የግራ ቀኙ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ መታየትና መወሰን ያለበት በቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች ነው በማለት ነው ። ለውሳኔውም መሠረት ያደረገው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 723/1/ የተጻፈውን ድንጋጌ ነው ። በዚህ ቁጥር በመተጫጨቱ ጉዳይ ወይም በመተጫጨት ውል መፍረስ ምክንያት የሚነሱትን ክርክሮች መርምረው ውሳኔ የሚሰጡ በመተጫጨቱ ሥርዓት ምስክሮች የነበሩት የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች እንደሆኑ ተደንግጓል ። የዚህ ድንጋጌ የአፈጻጸም ወሰን ግን ከቤተዘመድ የሽምግልና ዳኝነት ዓላማና በምዕራፍ ሁለት ስለመተጫጨት ከተጻፉት ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ መታየት ይኖርበታል ። ሕጉ የትዳር ጉዳይ በቅድሚያ በቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች እንዲታይ የሚያዘው ጋብቻ በቀላሉ እንዳይናድ ለመጋባት

የተስማሙ ወይም የተጋቡ ሰዎችን ለማስታረቅ ጥረት እንዲደረግ ፣ የማስታረቁ ሙከራ ካልተሳካም የቤተሰብ ምስጢር ይፋ ሳይወጣ ጉዳዩ በዘመዶቻቸው ወይም በቅርብ የሚያውቋቸው ሽማግሌዎች እንዲወሰን ታስቦና ታቅዶ ነው ። ለመጋባት የተስማሙ ገና ትዳር ላልመሠረቱ ሰዎች ግን ይህ ዓላማ ሙሉ በሙሉ ውጤት ይኖረዋል አንልም ። የተጫጩ ሰዎች ትዳር ለመመስረት ተስማሙ እንጂ ገና ቤተሰብ አላቋቋሙም ። ቤተሰብ ባለማቋቋማቸውም ይፋ መውጣት የለበትም የሚባል የቤተሰብ ምስጢር አይኖርም ። ምስጢር ሊኖር ቢችል እንኳ ይህን ያህል ከባድ ነው ተብሎ አይገመትም። መተጫጨትም በውል ዘንግ እንጂ በጋብቻ አቋም አይመደብም ። የውል ባህሪው የሚያመዝን በመሆኑም እንደ ተመሠረተና ተመስርቶም እንደተደላደለ ማኅበራዊ አቋም ተቆጥሮ በመተጫጨት ምክንያት የሚነሳ ክርክር ሁሉ ሁልጊዜ በቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች መታዬት ይኖርበታል አይባልም ።ማንኛውም ዓይነት በመተጫጨት ምክንያት የሚነሳ ክርክር ሁልጊዜ በቅድሚያ በቤተዘመድ የሽምግና ዳኞች መተዬት ይገባዋል እንደማይባል በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 573/2/እና 576 ከተጻፉት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። በቁጥር 573/2/የመተጫጨት መፍረስ ስለሚያስከትለው የሕሊና ጉዳት ስለሚከፈለው ካሳ የካሳውን ልክና ለመጠየቅ የሚችለውን ባለመብት ለመወሰን ፍርድ ቤቱ የአገሩን ልማድ መሠረት አድርጐ እንደሚከተል ተደንግጓል ።እንዲሁም በቁጥር576 በመተጫጨት መፍረስ ላይ ተመስርተው የሚቀርቡት ክሶች ሁሉ መተጫጨቱ ከፈረሰበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ የሚታገዱ ይሆናሉ ተብሎ ተነግሯል ። በቁጥር 573/2/ በተጻፈው ድንጋጌ መሠረት በመተጫጨት መፍረስ ምክንያት የሚጠየቀውን የሕሊና ጉዳት ካሳ መጠኑንና ማን መጠየቅ እንደሚችል ይወስን ተብሎ ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት እንጂ የቤተዘመድ የሽምግልና ጉባኤ አይደለም ። በቁጥር 576 « ክሶች » የሚለው ቃል መግባቱ በመተጫጨት ምክንያት የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደሚችል የሚያመለክት ነው ። ለቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች የሚቀርበው አቤቱታ እንጂ ክስ አይደለም ። በመተጫጨት ምክንያት የሚነሳ ክርክር ሁሉ በቅድሚያ ለቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች መቅረብ የሚገባው ቢሆን ኑሮ በቁጥር 573/2/ « ፍርድ ቤት » መጠቀሱ በቁጥር 576 ደግሞ « ክሶች » የሚለው ቃል መመረጡ አያስፈልግም ነበር ። ይህን ስንል ግን በመተጫጨት ምክንያት የሚነሳ ክርክር ሁሉ ምን ጊዜም ለፍርድ ቤት መቅረብ ይችላል ወይም መቅረብ ይገባዋል ለማለት አይደለም ። በቁጥር 723/1/ የተጻፈው ድንጋጌ ውጤት አልባ እንዳይሆንና በቁጥር 573/2/ እና 576 ከተጻፉት ድንጋጌዎች ጋር እንዲጣጣም ሆኖ ይተርጐም ከተባለ በመተጫጨቱ ምክንያት የሚቀርበው ክርክርና የሚጠየቀው ዳኝነት ምን እንደሆነ በቅድሚያ ተለይቶ መታወቅ ይኖርበታል ። የሚቀርበው ጥያቄ አንደኛው ወገን ለመጋባት ፈቃደኛ አልሆነምና ጉዳያችንን ሽማግሌ አይቶ አለመግባባታችንን አስወግዶና አስታርቆ የመተጫጨቱ ውል ውጤት እንዲያስገኝልን ወይም በሌላ አነጋገር ጋብቻችንን እንድንፈጽም ( ሙከራ ) ያድርግልን የሚል ከሆነ በእርግጥ እንደዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በቁጥር 723/1/ መሠረት ለቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች በቅድሚያ መቅረብ ይኖርበታል ። ነገር ግን ጥያቄው አንደኛው ወገን የመተጫጨት ውሉን ያለምክንያት አፍርሷልና ወጭዎችን ይክፈለኝ ፣ ስጦታዎችን ይመልስልኝ ፣ የሕሊና ጉዳት ካሳ ይክፈለኝ የሚል ከሆነ ይህ በመጀመሪያ ደረጃ ለፍርድ ቤት የማይቀርብበት ምክንያት የለም ። እንደዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ለቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች መቅረብ ያለበት አይመስለንም ። ጥያቄው የውልን አለምክንያት ማፍረስ የሚመለከት እንጂ አስታርቁን ፣ ጋብቻችንን እንድንፈጽም አድርጉልኝ የሚል አይደለም ።

በያዝነው ጉዳይም የይግባኝ ባዩ እጮኛ የጋብቻውን መፈጸም እንደማትፈ
ልግ ቀደም አድርጋ አረጋግጣለች ። ይግባኝ ባዩም የጠየቀው ከእጮኛዩ ጋር አስ
ታርቁኝ ፡ ጋብቻችንን እንድንፈጽም ሙከራ አድርጉልኝ ሳይሆን እጮኛውና የእ
ጮኛው ወላጆች የመተጫጨቱን ውል ያለበቂ ምክንያት ያፈረሱት ስለሆነ ወጭ
ዬን ክፈሉኝ ፡ ስጦታዬን መልሱልኝ ፡ የሕሊና ጉዳት ካሳ ክፈሉኝ የሚል ነው ።
እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ለቤተዘመድ የሽምግልና ዳኛ የሚቀርብበት ምክንያት አይ
ታየንም ። በተለይም በዚህ ጉዳይ ለመተጫጨቱ መፍረስ ኃላፊ ናት ተብላ ወጭ
ውንና ካሳ እንድትከፍል የተፈረደባት የታጨችው ሴት ሳትሆን እናትየዋ ናት ።
ታዲያ ይግባኝ ባይዋና የእጮኛው እናት የሆነችው መልስ ሰጭዋ የሚከራከሩበት
የገንዘብ ጉዳይ በቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች በቅድሚያ መታየት የሚገባው
ምን ውጤት ሊያስገኝ ነው ? ስለዚህ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሁለቱ ወገኖች ክር
ክር በቅድሚያ በቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች መታዬት አለበት በማለት የአው
ራጃው ፍርድ ቤትን ፍርድ በመሻር የሰጠው ውሳኔ ትክክል ስላልሆነ እንዳልተ
ፈረደ ሆኖ በሥረ ነገሩ አከራክሮ በበኩሉ ተስማሚ መስሎ የታየውን ውሳኔ ይስጥ
ብለናል ። በዚሁ መሠረት እንዲፈጸም የዚህ ውሳኔ ግልቤጭ ለከፍተኛው ፍርድ
ቤት ይተላለፍለት ። //

# የተጻፈ ሕግን ስለመተርጐም

## በፍትሐብሔር ይግባኝ ጉዳይ ቁጥር 1202/73 ላይ የቀረበ አስተያየት ፤

በወርቁ ተፈራ*

በዚህ እትም ላይ በቀረበው የፍትሐብሔር ይግባኝ ቁጥር 1202/73 ውስጥ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 723/1/ን (ከዚህ በታች ተመልክቷል) በመተርጎም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከአውራጃው ፍርድ ቤት በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ በመተጫጨት ውል መፍረስ ምክንያት የሚቀርበውን የካሳ ጥያቄ በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ለማየት ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ገልብጦአል ። በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በአጋጣሚ ለሚመለከተው ሰው በመተጫጨት ውል ላይ የሚነሳውን ክርክር ለመወሰን ሥልጣን ያለው ማን ነው ? ፍርድ ቤት ወይስ የቤተሰብ የሽምግልና ዳኞች ? የሚለውን ቀላል የሥነ ሥርዓት ሕግ ጥያቄ ብቻ የሚፈታ ይመስላል ። ጠለቅ ብለው ሲመለከቱት ግን በጉዳዩ የተሰጠው ውሳኔ በተጻፈ ሕግ አተረጓጐም ረገድ ያሉትን ቋሚ ደንቦች በሚመለከት አስተያየት ሊሰጥባቸው የሚገባ ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦችን የሚመለከት ሆኖ ይገኛል ።

በዚህ ረገድ ይህ ጉዳይ ቢያንስ የሚከተሉትን ሶስት ተከታታይ ጥያቄዎች ያስነሳል ።

1. የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 723/1/ ግልጽ ሆኖ ሳለ ወደ ትርጉም መሄድ ያስፈልግ ኖሮአልን ?
2. በፍርዱ የተሰጠው ትርጉም የተመሠረተበት ምክንያት ሲታይ ተቀባይነት ያለው ነውን ?
3. ፍርድ ቤቱ ለሕጉ በሰጠው ትርጉም መሠረት የተደረሰበት ውጤት ተፈላጊ ነውን ?

በዚህ አስተያየት ለእነዚህ ጥያቄዎች እንዳቀራረባቸው በተቻለ መጠን አጭር መልስ ለመስጠት ሙከራ ይደረጋል ።

የተጻፈው ሕግ ግልጽ በሆነ ጊዜ በአተረጓጎም ደንቦች መጠቀም አስፈላጊ አለመሆኑ ቋሚ የአተረጓጎም ደንብ ነው ።[1] ስለዚህም አንድ በጽሑፍ ያለ ሕግ መተርጎም የሚያስፈልገው አሻሚ ሲሆን ወይም ከሌላ የተጻፈ ሕግ ጋር ሲቃረን አለዚያም ጉዳዩን ያልሸፈነ ወይም እንደተጻፈው ቢፈጸም ተገቢ ያልሆነ እንደሆነ[2] ነው ። ፍርድ ቤቱ ለትርጉም ያጋለጠው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 723/1/ ከዚህ በላይ የተገለጡት ጉድለቶች የሉበትም ።

የፍትሐብሔር ሕግ 2ኛ መጽሐፍ 4ኛ ክፍል ምዕራፍ 9 ጋብቻን በሚመለከት በሚነሱ ክርክሮች ላይ የፍርድ ቤቶችንና የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞችን

* ተባባሪ ፕሮፌሰር ፥ ሕግ ትምህርት ቤት ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ።

[1] ጂ. ዊሊያምስ ፥ ለርኒንግ ዘ ሎው (5ኛ እትም 1954) ገጽ 87.

[2] ጆርጅ ክሪቺኖቪች ፥ « ስታቱተሪ ኢንተርፕሬቴሽን ኢን ኢትዮጵያ » ፥ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ፥ ቮልዩም 1 (1964 እ.ኤ.አ፥ ገጽ 315—323)

የመዳኘት ሥልጣን በአጠቃላይ ለይቶ አስቀምጦታል ። በመተጫጨት ውል ላይ የሚነሱትን ክርክሮች በሚመለከት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 722 እና ቁጥር 723 / 1 / የተወሰኑ ክርክሮች በፍርድ ቤቶች ፤ ሌሎች ክርክሮች ደግሞ በቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች እንዲታዩ እንደሚከተለው ያዛል ።

> ቁጥር 722 የመተጫጨት ሥነ—ሥርዓት ተፈጽሟል ወይም አልተፈጸመም ለማለትና ይህ መተጫጨት ይጸናል ወይም አይጸናም ብሎ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው ዳኞች ብቻ ናቸው ሲል ፤ ቁጥር 723/1/ ደግሞ በመተጫጨት ጉዳይ ውስጥ ወይም በመተጫጨት ውል መፍረስ ላይ የሚነሱትን ክርክሮች መርምረው ውሳኔ የሚሰጡት በዚሁ በመተጫጨቱ ሥርዓት ምስክሮች የነበሩት የቤተዘመድ የሽ ምግልና ዳኞች ናቸው ይላል ።

በእነዚህ ሁለት አንቀጾች ይዘት የተገለጠው ሃሳብ እንደ እንቁ ቁልጭ ያለ ግልጽ ነገር ነው ። ክርክሩ የመተጫጨት ውል መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ሲሆን ለፍርድ ቤቶች መቅረብና በነሱም መወሰን አለበት ። በምንም ሁኔታ ለሌላ አካል መቅረብ የለበትም ። ክርክሩ የመተጫጨት ውል መፍረስን ጨምሮ መተ ጫጨትን በሚመለከት ማናቸውም ሌላ ምክንያት ከሆነ ግን ለቤተዘመድ የሽ ምግልና ዳኞች መቅረብና መወሰን አለበት ። ሕግ አውጭው ከዚህ ግልጽ ከሆነ ሕግ በተለየ ሥርዓት እንዲፈጸም በፈለገ ቁጥር ይህንኑ ልዩ ሥርዓት በይፋ አው ጀአል ። ለምሳሌ የቤተሰብ የሽምግልና ዳኞች በአእምሮ ግምት በቂ በሆነ ጊዜ ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሳይሰጡ የቀሩ እንደሆነ በነሱ ሥልጣን ክልል እንዲሆን በሕግ በተፈቀደው ክርክር ላይ ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዲቀዳጅ ተደንግጓል ።[3] እንዲሁም ብተወሰኑ ጠባብ ምክንያቶች ይግባኝ ለፍርድ ቤት እንዲቀርብ በግ ልጽ ተፈቅዷል ።[4] ከዚህ በተረፈ ለፍርድ ቤት እንዳይቀርቡ በግልጽ ወይም በነ ገሩ አዝማሚያ ቡተከለከሉ አሁን ያያዝነውን ጉዳይ በመሰሉ ክርክሮች ላይ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ከመቀዳጀት ታግደዋል ።[5] ስለዚህ ከዚህ በላይ የተገለጠውን ስንመለከት የቁጥር 723 / 1 / ን ትርጉም ለመረዳት ወደ ሕግ መተርጎሚያ ዘዴ ዎች መራመድ የሚያስገድድ ምክንያት አልነበረም ።

ፍርድ ቤቱ ግን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 723 / 1 / ን ድንጋጌ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 572 / 2 / እና ቁጥር 576 ጋር በማነጻጸር በመጀመሪያውና በኋለኞቹ ሁለት ድንጋጌዎች መካከል ያልተጣጣመ ነገር አለ በማለት እነዚህ ድንጋጌዎች ይጣጣሙ ዘንድ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 723 / 1 / ን ድንጋጌ በእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ይዘት መሠረት መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል ።

> ቁጥር 573 / 2 / « የዚህን ካሳ ልክ ለመወሰንና ካሳውንም ለመጠየቅ የሚችለውን ባለመብት ዳኞች ( ስርዝ የተጨመረ ) የአገሩን ልማድ መሠረት አድርገው ይከተላሉ » ይላል ። ቁጥር 576 ደግሞ « በመተ ጫጨት መፍረስ ላይ ተመስርተው የሚቀርቡት ክሶች ( ስርዝ የተጨ መረ) ሁሉመተጫጨቱ ከፈረሰበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ የሚታገዱ ይሆናል » በማለት ያብራራል ።

የመተጫጨት ውል በመፍረሱ ምክንያት የሚነሱ ክርክሮችን ለመስማት ሥልጣን ያለው የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኝነት ጉባዔ መሆኑ በቁጥር 723 / 1 /

3 የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 737
4 የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 736
5 የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ—ሥርዓት ቁጥር 4

ላይ በግልጽ ቢደነገግም የፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 573 / 2 / ውስጥ « ፍርድ ቤት » ፤ በቁጥር 576 ውስጥ ደግሞ « ክሶች » በሚሉት ቃላት መጠቀሙ ፍርድ ቤትም በመተጫጨት ውል መፍረስ ምክንያት በሚነሱ ክርክሮች ላይ ሥልጣን ያለው መሆኑን ያመለክታል በማለት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትንተና አድርጓል ። ይህ ባይሆን ኖሮ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ « ፍርድ ቤት » በሚለው ፈንታ » የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች » ፤ « ክስ » በሚለው ፈንታ « አቤቱታ » በሚሉት ቃላት ሕጉ በተጠቀመ ነበር በማለትም ሃሳቡን አጠናክሯል ። ይህ የፍርድ ቤቱ አመለካከት በእንግሊዝኛው የፍትሐብሔር ሕግ ቅጅ ውስጥ በተከሰተው የትርጉም ስህተት ላይ የተመሰረተ ይመስላል ። በቁጥር 573 / 2 / ውስጥ በእንግሊዝኛው ቅጅ « Courts » በተባለው ቃል የመሥሪያ ( ኦፊሲየላዊ/ቋንቋ በሆነው የአማርኛው ቅጅ ውስጥ « ዳኞች » የሚለው ቃል ነው ። ሕጉ በተረቀቀበት የፈረንሳይኛው ቅጅም እንደዚሁ ፍርድ ቤት ( Courts ) በሚለው ሳይሆን ዳኛ ( Judge ) የሚለውን ቃል ነው የተጠቀመው ። ጉዳዩ እንደዚህ በመሆኑም በቁጥር 573 / 2 / እና በቁጥር 723 / 1 / መካከል እውን የሆነ ቅራኔ የለም ። በቁጥር 573 / 2 / የሠፈረው ድንጋጌ የሚመለከተው ሁለቱንም ማለትም የቤተሰብ የሽምግልና ዳኝነት ሽምጋዮችንና የፍርድ ቤት ዳኞችን ነው ። በሥልጣናቸው ክልል የሆኑ እንደዚህ ያሉ ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ በሚያዩበት ጊዜ የቤተሰብ የሽምግልና ዳኞች በእነዚህ ቁጥሮች ድንጋጌዎች መሠረት ይሠራሉ ። ፍርድ ቤቶችም በይግባኝ ለሚቀርቡላቸው ጉዳዮችና በሕጉ በተደነገገው መሠረት በተወሰነ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲያዩዋቸው በሚመጡላቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት በእነዚሁ በጠቀስናቸው ቁጥሮች ድንጋጌዎች ይጠቀማሉ ።

« ክስን ማቅረብ » / ቁጥር 576 / ፣ « የተነሱትን ክርክሮች ማሰማት » / ቁጥር 723 /1 / / እና « አቤቱታን ማሰማት » / ቁጥር 727 / በሚሉት ሐረጎች መካከል የልዩነት ወሰን በማበጀት የተሰጠው ትንታኔም የሚያዘልቅ አይደለም ። ይህን አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ምክንያት የቤተሰብ የሽምግልና ዳኞች የሚያስተናግዱት « አቤቱታዎችን » / Petitions / እንጅ « ክሶችን » /Actions) አይደለም ፤ « ክሶች » የሚለው ቃል በቁጥር 576 መስፈሩ በመተጫጨት ውል መፍረስ ምክንያት የሚነሱ ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ እንዲታዩ ለፍርድ ቤቶች መቅረብ የሚችሉ መሆናቸውን ይጠቁማል የሚል ነው ። የጠቀስናቸው ቃሎች አብዛኛውን ጊዜ አንዱ በሌላው እግር በመተካካት የሚያገለግሉና የሚያዝሉትም ትርጉም አንድና ተመሳሳይየሆነ ነው ። ይኸውም ክስን ማቅረብ ማለት ነው ። ለምሳሌ ከባለቤቴ መፋታት ይገባኛል በማለት ፍችን የሚፈልግ የአንድ ሰው ጥያቄ ክሱን ያቀረበው ለቤተሰብ የሽምግልና ዳኞችም ይሁን ወይም ይህ በሌለበት ለፍርድ ቤት ቢያቀርበው ምንም ልዩነት ሳይኖር የሰውየው የፍች ይገባኛል ጥያቄ በሁለቱም ቦታ « የፍች አቤቱታ » በሚል ይጠቀሳል ። በሌላ በኩል ደግሞ ጥያቄው የቀረበው ለቤተሰብ የሽምግልና ዳኞችም ቢሆን እንኳ የጉዳት ካሣ ክፍያን አስመልክቶ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እንደምናውቀው « አቤቱታ » ( Petition ) በሚለው ቃል ማንም አይጠይቀምም ። እነዚህ ሐረጎች ክሶችን ማቅረብ ከሚል ትርጉም በቀር ሌላ የሚጠቁሙት ነገር ቢኖር ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ከተሰጠው መድረክ ይልቅ የክሱን ባህሪ ብቻ ነው ። በአንድ ወገን በቁጥር 573/2/ እና ቁጥር 576 በሌላ ወገን ደግሞ በቁጥር 723 /1/ ባላቸው የቃላት አጠቃቀም ቅራኔ አለ ብንልም እንኳ ግልጽ የሆነውን የቁጥር 723 / 1 / ን ትርጉም ለመለወጥ በቁጥር 573 / 2 / እና በቁጥር 576 ድንጋጌዎች ትርጉም ተመርኩዞ መነሳት ትክክል አይሆንም ። ቁጥር 573 / 2 / እና

ቁጥር 576 ከቁጥር 723 /1/ ጋር ጎን ለጎን ሲታዩ ጉዳዮችን ለማየት ስላለው የሥልጣን ወሰን ምንም ነገር አያነሱም ። ቁጥር 573 /2/ የሚ ለከተው የጉዳት ካሳውን ክፍያ መጠን መወሰንና ይህንን ክፍያ ለመጠየቅ ባለመብቱ ማን እንደሆነ ነው ። ቁጥር 576 በጉዳዩ ላይ የሚነሱት ክሶች እስከመቸ መቅረብ እንዳለባቸው የሚገልጸውን የጊዜ ገደብ ነው የሚሰጠው ። ቁጥር 723 /1/ ግን የመተጫጨት ውል መፍረስን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት ሥልጣን ያለው ማን እንደሆነ ይወስናል ። የትርጉም አለመጣጣም በሚኖርበት ጊዜ « ልዩ ድንጋጌ ከአጠቃላይ ድንጋጌ ቅድሚያ ይኖረዋል » የሚለውን የአተረጓጎም ደንብ መከተል ካለብንና በመተርጐም መፍትሄ የምንሻለት አንድን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ጥያቄ ከሆነ ፣ ቁጥር 573 /2/ እና ቁጥር 576 ናቸው እንጂ በቁጥር 723 /1/ ድንጋጌ መሠረት መተርጐም ያለባቸው የተገላቢጦሽ መሆን የለበትም ። በዚህ መልክ ሲተረጐም በቁጥር 573 /2/ የተጠቀሰው «ፍርድ ቤት» ወይም « ዳኞች » የሚለው ቃል በቁጥር 723 /1/ መሠረት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ችሎት ( ወይም የችሎት ዳኞች ) ማለት እንጂ ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም ። በቁጥር 576 የተጠቀሰው « ክሶች » የሚለው ቃልም ቢሆን እደዚህ ላሉት መድረኮች አቤቱታን ማቅረብ ማለት እንጂ ሌላ ትርጉም አይኖረውም ።

የሕግ አውጭውን ፍላጐትና የሕጉን ዓላማዎች አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ እያነሳ በተነተናቸው ነጥቦች ላይ ምንም ተቃውሞ የለንም ። ነገር ግን የመተጫጨቱ ውል በመፍረሱ ምክንያት የተነሳው ክርክር ስጦታዎችን ለማስመለስና የጉዳት ካሳ ክፍያን ለማግኘት ከሆነ የተጠቀሱት የሕጉ ዓላማዎች ጠቀሜታ አይኖራቸውም የሚለው የፍርድ ቤቱ ትንተና ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም ። ለመተጫጨቱ ውል መፍረስ መንስኤውንና ለመፍረሱ ተጠያቂ የሆነውን ወገን ለማወቅ የአጥፊ ነህ አጥፊ አይደለሁም ክርክር በእጮኞች መካከል ይካሄዳል ። በዚህም ክርክር በህዝቡ ከመታወቅ ይልቅ በቤተሰቡ ክልል ተወስነው ቢቀሩ የሚበጁ ጉዳዮች ይፋ ሊወጡ ይችላሉ ። የተጣሉ እጮኞችን በሚቋቋሙት የቤተሰብ የሽምግልና ዳኞች ጥረት ማስታረቅ የመቻሉ ሁኔታም ቢሆን በፍጹም የማይሆን ነው ተብሎ ሳይሞከር ሊገደፍ የሚገባው አይደለም ። ጠበኞችን ማስታረቅ መቻሉ እውነትም የመነመነ ነው ብለን እንኳ ብንቀበል፤ ሕጉ ለቤተሰብ የሽምግልና ዳኞች ሥልጣን በሚሰጣቸው ጉዳዮች ሁሉ የእነዚህ የሕጉ ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ አለመገልገል ሕጉን እንዳይሠራበት አያደርገውም ። ሕጉ ተፈጻሚነት የሚያጣው በተግባር ስንተረጉመው በጥቅሉ አግባብ ወደሌለው ማለት ፍትህ አልባ ( Unreasonable) ወደሆነ ውጤት ሲመራን ነው ። የመተጫጨት ውል በመፍረሱ ምክንያት የሚነሱ ክርክሮች በሽምግልና ዳኞች መታየታቸው ደግሞ ያን ያህል አግባብ ወደሌለው ውጤት የሚመራን አይሆንም ። የሕግ አውጭው ፍላጐት ግልጽ ነው ። ይኸውም ቤተሰብን ገና ከውጥኑ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ግቡ ሊያጋጥሙት ከሚችሉ በፍርድ ቤቱ ከተገለጡት ጉዳዮች ለመጠበቅ ነው ። ይህን ውጤት ለማግኘትም የመተጫጨት ውል መፍረስን ጨምሮ የተወሰኑ ቤተሰባዊ አለመግባባቶች ( የተወሳሰበ የሕግ ትርጉም ጉዳይ በማይኖርበት ጊዜ ) መፍትሄ በቤተሰብ ክልል እንዲወሰን ለማድረግ ተሞክሯል ። እንደዚህ ባይሆን ኖሮ የመተጫጨት ውል ስለግዴታዎች በአጠቃላይ በሚደነግገው የሕጉ አካል በተጠቃለለ ወይም ልዩ ውሎችን በሚመለከተው የሕጉ ክፍል እንዲገባ በተደረገ ነበር ። የመተጫጨቱ ውል በቤተሰብ ሕጉ ክፍል ውስጥ መግባቱ እራሱ ገና በጅምር ላይ ያለው ቤተሰብ ተመስርቶ ለተደላደለው ቤተሰብ የሚያስፈልገውን ያህል ጥበቃ ሊደረግለት እንደሚገባ ያሳያል ። ስለዚህም ፍርድ ቤቱ መተጫጨ

ትን ከቤተሰብ ሕግ ጋር ሳይሆን ከውል ሕግ ጋር መድቦ ማየቱ በሕጉ አቀነባበርና አነዳደፍ ላይ ከሚታየው ከሕግ አውጭው ፍላጐት ጋር የሚጣጣም አይደለም ።

በመጨረሻም ለዚህ ጉዳይ የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ ከተከተልን በመተጫጨት ውል መፍረስ ምክንያት የሚነሳን ክርክር ለማየት ሥልጣን ያለው ማን ነው የሚለው ጥያቄ መልስ በፍትሐብሔር ሕጉ በቁጥር 723 / 1 / በግልጽ በተደነገገው የሥልጣን አመዳደብ ሳይሆን ከሳሹ በተከሳሹ ላይ ሊፈረድልኝ ይገባል ብሎ ባቀረበው ጥያቄ ዓይነትና ጉዳዩ ወደ የቤተሰብ የሽምግልና ዳኞች ቢቀርብ ለቤተሰቡ ጥበቃ ያገለግላሉ ተብለው የታሰቡት ውጤቶች ስኬት ያገኛሉ ወይስ አያገኙም በሚሉት ሀሳቦች ላይ የሚመሠረት ይሆናል ። ይህ ደግሞ የማይሠራና የማያስፈልግም ነው ። አይሠራም የሚያሰኘውም ምክንያት ጋሪውን ከፈረሱ በፊት የሚያስቀምጥ በመሆኑ ነው ። ከሳሽ ተከሳሽ የክርክር ማመልከቻዎችን ከመለዋወጣቸውና የክርክር ነጥባቸውን ከመመልከቱ በፊት ጉዳዩን የሚዳኘው አካል እነዚህን መመዘኛዎች ሙሉ በሙሉ ለመረዳት አይችልም ። የማያስፈልግ ነው የሚያሰኘውም በሕጉ ላይ የማያስፈልግ ጥርጣሬ የሚፈጥርና ይህም ዋጋቢስ ወደሆነ የሥነ ሥርዓት ጭቅጭቆች የሚያመራ በመሆኑ ነው ።